# ሰሞነኛ (9)

## «ግንቦት የሟርት ሳይሆን የድልና የግንባታ ወር ነው፡፡»

## በሎስአንጀለስ የኢትዮጵያ ቆንስላ ጄኔራል ጽ/ቤት

**ግንቦት/2009**

**May/2009**




**Consulate General of Ethiopia**

**3460 Wilshire Blvd # 308**

**Los Angeles, CA 90010**

**Tel: 213 365 6651 Fax: 213 365 6670**

www.ethioconsulate-la.org

# ግንቦት የሟርት ሳይሆን የድልና የግንባታ ወር ነው፡፡

የኢትዮጵያ  ህዝቦች ግንቦት በተነሳ ቁጥር አስከፊ የጭካኔና የግድያ ዘመን ማክተሚያ አድርገው ያስታውሱታል፡፡ በአገራችን የአዲስ ስርዓት ግንባታ መባቻ በመሆኑ ግንቦት የነፃነት ተመሳሌነቱን እንደጠበቀ ይሄው ለ18ኛ ጊዜ ተዘክሯል፡፡ ታድያ ግንቦት በመጣ ቁጥር በባዶ እጅ ሳይሆን በአዳዲስ የልማት ፣የማህበራዊና ፖለቲካዊ ድሎች እያጀብን መሆኑን ላየ ይህቺ አገር ካለመችው የዕድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ እንቅፋቶችን ሁሉ የመመከት ብቃት እንዳላት ማረጋገጥ ይችላል፡፡

የዘንድሮው ግንቦትም እንዳለፉት 17 አመታት ግንቦቶች ሁሉ አፍን ሞልተው ሊጠቀሱ የሚችሉ ግዙፍ የግንባታ ፕሮጀክቶች የተመረቁበት ነበር፡፡ በአዲስ አበባ የጎተራን ተላላፊ መንገድ ጨምሮ 6 አውራ የመንገድ ግንባታዎችን ሲያስመርቅ፣የግልገል ግቤ 2፣የተከዜና በለስ ሀይድሮ ኤሌክትሪክ ግድቦችን የመጠናቀቂያ የመጨረሻ ምዕራፍ የሰማንበት ነው፡፡ ስለዚህ ግንቦት የልማት ግንባታዎቻችን መነሻ ብቻ ሳይሆን አሁንም በጅምር ላይ ያሉትን የልማት ተግባሮቻችን ይበልጥ ለማሳለጥ እንደገና ቃል ኪዳናችን ያደስንበት ሆኖ ነው ያለፈው፡፡

የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ግንቦት የነፃነትና የእኩልነት ድላቸው መነሻ በመሆኑ በየክልሎች የተጀመሩ የልማት፣የዴሞክራሲና የሰላም ተግባራትን በማከናወን ወሩ ይበልጥ እንዲደምቅ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ የኢትዮጵያ ህዝቦች በየአካባቢያቸው፣ድህነትን ለማስወገድ እያደረጉ ያሉት ትንንቅ ወደ ዕድገት የምናደርገውን ጎዞ የተሳካ እንደሚሆን አመላክቷል፡፡

እንደ ጋምቤላ ፣አፋር (ሰመራ) ሶማሊ (ጅጅጋ)፣ቢኒሻንጉል (አሶሳ) የመሳሰሉ ታዳጊ ከተማዎችና የአስተዳደር ቦታዎች ድሮ ከሚታወቁበት ዳር አገርና ጠፍ ቦታ ምሳሌነት ወጥተው ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝቦች ሰላምን ተንተርሰው ፣ተስፋን ሰንቀው ፣ተግተው ከሠሩ ሊደርሱበት የሚችሉትን የዕድገት ርቀት ፈር አመላካች ሆኗል፡፡ከዚህም ተነስተው እነዚህ ህዝቦች ግንቦትን የነፃነታቸውና የእኩልነታቸው መሰረት አድርገው ያከብሩታል፡፡

ግንቦት የአሮጌ አስተሳስብ ማክተሚያ መሆኑ ብቻ ሳይሆን የአዲስ አስተሳስብና የዴሞክራሲ ስርዓት ጅምር ማሳያ ነው፡፡ ግንቦትን ተንተርሶ የዛሬ 18 ዓመት በፊት በሰኔ ላይ የተመሰረተው የሽግግር መንግስት በሰላማዊ መንገድ ለአገራችን እንሰራለን የሚሉ

አካላትን ያሰባሰበ፣ በአገራቸው ጉዳይ ድምፃቸውን እንዲያሰሙ መንገዱን ያመቻቸና የዴሞክራሲ ስርአት ምስረታችን የመጀመሪያውን ችግኝ የተከለ ነበር። በርግጥ በዚህ የሽሽግር መንግስት ተሳትፎ ሰላማዊ መንገዱ ያልጣማቸው አካላት እድሉን ሊጠቀመቡት አለመቻላቸው፣ በዴሞክራሲ ስርአት ግንባታችን ላይ መጠነኛ ዕንቅፋት ቢሆንም፣ አይነተኛ ጉዞውን ሊያስተጓጉሉት ግን አልተቻላቸውም።

የዘንድሮው ግንቦት ሀያ አለማችን በኢኮኖሚ ቀውስ እየተላጋች በምትገኝበትና ይሄው ቀውስ አገሮችን ሳይመረጥ በሚንጥበት ጊዜ የሚከበር ነው።አገራችን ከኢኮኖሚ ወጀቡ የሚተርፋት ጉዳት ባይታጣም ለመቋቋም የሚያስችል ዓቅም እንዳላት የታየበት ሆኗል። መንግስታት በኢኮኖሚው ዕድገት የሚኖራቸውን የተባ ተሳትፎ የሚቃወም አስተያየት ያላቸው ሰዎች፣ በተለይ አገራችን በግብርና ልማት፣ በኮንስትርክሽን መስክ፣ እንዲሁም በፋይናንስ ተቋማት መረጋጋት ዙሪያ የተከተለችቸውን የፖሊሲ ዕርምጃዎች አሁን የታየውን የኢኮኖሚ ሞገድ መቋቋም እንደተቻለ መቀበል ችለዋል። የአገራችን ለጋ የኢኮኖሚ አቅምን የበለጠ ለማጠናከር መንግስት በተጠናና በተመረጠ መልክ በኢኮኖሚው ውስጥ ሲያደርግ የቆየውና እያደረገ ያለው ተሳትፎ ለተደጋገፈና ለተወራረሰ ኢኮኖሚዊ እድገት ትክክለኛ መንገድ መሆኑን በማስመስከር ላይ ይገኛል።

ግንቦት ከላይ የጠቀስናቸው አውራ ጉዳዮችን ብቻ ሳይሆን ለመዘርዘር ብዙ የሆኑ ሰፊ ተግባራትን የጀመርነበት፣የወጠንበት፣ ዕድገት ያስመዘገብንበትና የዘከርንበት ወር ነው። ከዚህ በተጨማሪ የኢትዮጵያ ህዝብ በረዥሙ ትግሉና በከፈለው መስዋእትነት የተጎናፀፈውን የዴሞክራሲ ድል በጎዳና ግርግርና የመንገድ ላይ ነውጥ በማካሄድ የዴሞክራሲ ሀዲዱን እንዲለቅና ህዝቦች እንዲተላለቁ የተወጠነብንን ሽብር በህዝብ ተሳተፎ ያከሸፍነው በዚሁ በግንቦት ወር ነው።

በመሆኑም ግንቦት ባለፉት 18 ዓመታት ለኢትዮጵያ ህዝቦችና መንግስትና የነፃነት ምሳሌ፣የእኩልነት ፋና ወጊ ሆና በተገኙ ሁለገብ የዕድገት ድሎቻችን ደምቆ የያልተከበረበት ጊዜ የለም ።ይህን በውል ያልተገነዘቡ ጥቂት አካላት ግንቦትን የቅዠታቸው መዳራሻ የሚርታቸው ማዳመቂያ ለማድረግ ሲጥሩ ይታያሉ። ግንቦት ለአገራችን ህዝቦች ያመጣውን ጥቅም እያዩ ላለማስተዋል፣እየሰሙ ላለማዳመጥ ይጥራሉ።ከዚያ ይልቅ የግንቦት ልደታን አጉል ተሰፋ ቋጥራው መናፍስትን በማመን የኢትዮጵያን መንግስትን እንዲጥልላቸው የጥላቻ ንፍሮን ይበተናሉ።የዘንድሮው ግንቦትም የእኛን የልማት ብስራት አጉልቶ የእነርሱን ሟርትና ምኞት በማብነን ወሩ ተሸኝቷል።የሚቀጥለው ግንቦት የድል ወር እንዲሆን እኛ በተግባር ደፋ ቀና ማለት

ይዘናል፡፡የግንቦትን መናፍስት ያመኑ ደግሞ ሌላ መዓት ሌላ ግርግር እንዲመጣ በማሰብ በግንቦት ወር ያሟርታሉ፡፡

ግንቦት ለኢትዮጵያ ህዝብ የልማትና የእኩልነት እንጂ የመተት ምሳሌ አለመሆኑን በምናስመዘግባቸው የለውጥ ተግባራት ለማስመክር አዲስ ወኔ የሰነቅን ሲሆን ፣ሟርተኞች ደግሞ ግንቦት መዓቱን እንዲያወርድላቸው ያመኑትን የግንቦት መናፍስት መለማመን ይዘዋል፡፡ ሟርትን ያመነ ጉም የዘገነ እንዲሉ፣ በመናፍስት ፈረስ ቅኝት የለውጥ ደንገላሳ መምታት የከጀላቸው ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች ወርሀ ግንቦት የግርግር ሳይሆን የግንባታ ዘመን ፈር መቅደጃ ነው እንላለን ፡፡